


# ድብቅ አደጋዎች







መስከረም 2017
ቅፅ ፬ | ቁጥር ፫

ንስንስ ትኩረቷን በLBQ ላይ አድርጋ በየሩብ ዓመቱ በኩዊር ኢትዮጵያ የምትታተም መጽሔት

Nisnis - A quarterly magazine published by Queer Ethiopia focusing on LBQ issues

# QUEER ETHIOPIA
## ኲዌር ኢትዮጵያ

«ኲዌር ኢትዮጵያ» የተለያዩ ፆታዊና ወሲባዊ ዝንባሌ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኲዌር ሴቶች እንዲሆን ታስቦ በኲዌር ሴቶች የተመሠረተ አማራጭ ምኅዳር ነው። ይኸውም ሌዝቢያን፣ ባይሴክሽዋል ወይም ኤሴክሽዋል የሆኑ ሴቶችንንና ትራንስ ሴቶችን ያካትታል። ይህ ምኅዳር የኲዌር ማኅበረሰብ ታሪክ እና የሕይወት ልምድ ትልቅ ሥፍራ የሚይዝበት ነው። እንደ ' ኲዌር ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ገጠመኞች፤ የተለያዩ ሰዎችን የግል ታሪኮች፤ ቃለ- መጠይቆች እንዲሁም ሥነ-ጥበባትን እንደምናካትት ተስፋ እናደርጋለን። ከነዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ እና በዳያስፖራ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ራሳቸውን ሆነው የሚመጡበት የበይነ-መረብ ማኅበረሰብ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል ፍላጎታችን ብቻ ሳይሆን ጥረታችንም ጭምር ነው።


queerethiopia.com

ethioqueer

QueerEthiopia

etqueerfamily@gmail.com

t.me/queeret


facebook
Queer Ethiopia
Unity Breaks Hate

# ማውጫ



03



04 - 11




12 - 17



18 - 21



22 - 25



26 - 29



30 - 33

ጥንቃቄ
የተሞላባቸው
ስብሰባዎች
34 - 36

"አንድ ሰው
የውሸት ማንነት
ይዞ እያታለለን
መሆኑን በምን
ማወቅ ይቻላል?
37 - 40

# የአርታዒያን መልዕክት

እንኳን ወደ 13ኛው የንስንስ እትም በደህና መጡ፡፡ በዚህ  በኢትዮጵያ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ወሳኝ የህይወት እውነታዎችን እንመለከታለን፡፡  ስለካትፊሽ፣ መጋለጥ፤ የስም መጥፋት እና  የመንግስት ክትትል አይነት ያሉ የኢትዮጵያ ኤልጂቢቲኪው+ ማህበረሰብን ደህንነት እና ጤና ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩ ርዕሶችን እንቃኛለን። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደ ማህበረሰብ እያጋጠመን ካለው ጥላቻ አንፃር እነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች የበለጠ አሳሳቢ ሆነዋል።

እነዚህ ጉዳዮች ከባድ ቢሆኑም ከአደጋነታቸው ባለፈ ጽናትን ያመላክታሉ፡፡ የእትማችን ልዩ አምድ የተለያዩ ማስፈራራቶች ስለደረሰባቸው አምስት ሰዎች ይዳስሳል፡፡ እነዚህ ታሪኮች ስለሚያጋጥሙን ተግዳሮቶች ከማስታወሳቸው ባለፈ በምንጋራቸው ችግሮች ውስጥ ያለውን ጥንካሬ እና መተሳሰብ እንድናስብ ያደርጉናል፡፡

ካትፊሽ መደረግ እና መጋለጥ እምነትን የሚሸረሽር እና ፍርሃት የሚያጭር ነው፡፡ አንድ ባለታሪካችን እንደምትጠቅሰው የማህበረሰባችን ትብብር እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ሌላ ባለታሪካችን ከመጋለጥ ስለመትረፋቸው እና ያልተጠበቀ ድጋፍን ከጓደኞቻቸው ስለማግኘታቸው ይነግሩናል፡፡ ሌላዋ ደግሞ በሀሰት የቀረባትን ሰው ስለማግኘትዋ እና ጥንቃቄ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ትነግረናለች፡፡

እንደኢትዮጵያዊ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ማህበረሰባችን የሚገኘው በኢንተርኔት ላይ ነው ይህም ለደህንነታችን ማድረግ የሚገባንን ጥንቃቄ ይበልጥ አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡ ስለዲጂታል ዲቶክሲንግ ወይም ኢንተርኔት አጠቃቀምን መቀነስ በሰራነው ታሪክ ሌሎች የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎችን ስናገኝ ማንነታችን መጠበቅ ከምንም በላይ ጠቃሚ እንደሆነ ያስታውሰናል፡፡ እነዚህ ታሪኮች ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት ሳናቋርጥ ምን አይነት የጥንቃቄ መንገዶችን መከተል እንዳለብን ያስረዱናል፡፡

በዚህ እትም የተካተተው ኢንፎግራፊክስ ስለ ኢንተርኔት ደህንነት፤ ዲጂታል ሴኪዩሪቲ፤ እና በህይወት የሚያጋጥሙንን የተለያዩ ነገሮች እንዴት መጋፈጥ እንዳለብን መረጃ ይሰጠናል፡፡ አደጋን እንዴት መለየት እንደምንችል እና ጥንቃቄ የተሞላበት ግንኙነት በማህበረሰባችን ውስጥ ማኖር እንደምንችል ያሳየናል፡፡

እነዚህን ችግሮች ስንጋፈጥ ለብቻችን አለመሆናችንን ማስታወስ አስፈላጊ ነው፡፡ በባለታሪኮቻችን የታየው ጽናት ማህረሰባችን ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ የሚያሳይ ምሳሌ ነው፡፡ ብዙ ችግሮች ቢያጋጥሙንም ታሪካችንን በማካፈል እና በመደጋገፍ ልንወጣው እንደምንችል ያሳየናል፡፡

ይህ የንስንስ እትም ጥሪ የምናቀርብበትም ነው፤ እነዚህ ከባድ ሁኔታዎች ስናሳልፍ በማወቅ እና በአብሮነት እንዲሆን እናስታውሳለን፡፡

እንደሁሌው ባለታሪኮቻችንን ገጠመኞቻቸውን ስላጋሩን፤ አንባቢዎቻችን ደግሞ ሁሌም ከጎናችን ስላሉ ምስጋናችን ከልብ ነው፡፡ ድጋፋችሁ እነዚህን አስፈላጊ ታሪኮች እንድንጋራ አስችለውናል እና እናመሰግናለን፡፡





# አደጋን መጋፈጥ

# Resilience of queer people in a hostile environment

የኢትዮጵያውያን ኤልጂቢቲኪው+ ግለሰቦች በኢትዮጵያ ያለውን የጥላቻ የተሞላ ማህበረሰብ ውስጥ ሲኖሩ ያጋጠሟቸው ነገሮች ምንድናቸው? ሃሰተኛ ማንነት በመያዝ ማጭበርበር፣ ያለፈቃድ የአንድ ሰውን የግል መረጃን ኦንላየን በመልቀቅ እና በቋሚነት የአንድ ሰውን ፍትወተ ዝንባሌ እና ጾታዊ ማንነት በማጋለጥ ዛቻ ታሪኮቻቸው አማካኝነት ኩዊር ሰዎች ግንኙነትን በመፈለግ ላይ የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች እናያለን። ነገር ግን በነዚህ አደጋዎች መካከል የእነርሱ ጥንካሬ እና የማህበረሰቡ ድጋፍ ያበራል፤ ይህም በእውነተኛነት ለመኖር የሚያስፈልገውን ድፍረት ያሳያል።

በኮሮና ወቅት ነበር። እናም በዛ መሰባሰብ በማይቻልበት ወቅት ሳባ የሰው ፍቅርን ፈለገች። ውስጧ የሆነ ነገር ልክ እንዳልሆነ ቢነግራትም ቲንደር ላይ ካገኘችው ሰው ጋር ማውራት ቀጠለች።

ወሬያቸው ወደቴሌግራ ሲዘዋወር ደግሞ በይበልጥ መተማመኗ ጨመረ። ንግግራቸው ሲቀጥል፤ ጭንቀቷ ጨመረ፣ ነገር ግን እውነተኛ ግንኙነትን ብሎም በአካል መገናኘትን እንደሚያመጣ ተስፋ ነበራት።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግለሰቡ የራቁት ምስል እንድትልክ ጠየቀ። አልተስማማችም፤ ያ ሰው ግን ሊተዋት ፈቃደኛ አልነበረም "ፎቶሽን ለጥፌ አጋልጥሻለሁ" በማለት ያስፈራራት ጀመር።

ከዚህ በፊት ብዙ ማስፈራሪያዎችን በማስተናገዷ "ትክክለኛ ፎቶዬን ያገኘህ ከመሰለህ ተሳስተሀል" ስትል መለሰችለት። ከዚህ በፊት ካጋጠሟት ነገሮች በመማር አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጋ ነበር። ከስልኳ እና የውሸት ፎቶዋ ጀርባ በመደበቋ ደህንነት ተሰምትዋት ነበር። ይሁንና ግለሰቡ ትክክለኛ ፎቶዋን ላከላት። "እንዴት ፎቶዬን እንዳገኘው አላውቅም፤ ቴሌግራሜ ስለራሴ ያለውን መረጃ እንዳያሳይ አድርጌው ነበር።" ትላለች፡

ከረፈደ ነበር ያ ሰው ሌዝቢያን እንደሆነ የሚያስመስል ወንድ መሆኑን ያወቀችው። ለቀናት ምን ሊያደርግ እንደሚችል በማሰብ ተጨነቀች። ፎቶዋን ፖስት ያረገው ይሆን፤ የት ነው የሚለቀው፤ ለሌሎች ተናግሮ ቴሌግራሟን ያጋራል፤ ጭንቀት ውስጥ ነበረች።

በመጨረሻ የቴሌግራም አካውንትዋን አጥፍታ እንዳያደርገው መፀለይ ጀመረች።

በሚያሳዝን ሁኔታ የሳባ ታሪክ ልዩ አይደለም በኢትዮጵያዊ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች ዘንድ ያለውን የተለመደ ችግር የሚያመላክት ነው። ሳባ እንደምትለው "በእኛ ማህበረሰብ ካትፊሽ ያልተደረገ ሰው በጣም ጥቂት ነው።" ካትፊሽ መደረግ፣ መጋለጥ፤ የስም መጥፋትና ሌሎችም ችግሮች  የኢትዮጵያ ኤልጂቢቲኪው+ ማህበረሰብ ያለበትን አደጋ የሚያመላክት ነው።

የሳባ ታሪክ የኦንላይን ግንኙነቶች ያለውን አደጋ ያሳየናል። በሌላ በኩል የሰላም ታሪክ ደግሞ በአካል ራሱ ባለ ትውውቅ ድብቅ ወጥመድ ሊኖር እንደሚችል ይነግረናል።

ሰላም፡ የደህንነት ቅዠት

በአዲስአበባ ለምትኖረው የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዋ ሰላም፤ የደረሰባት ማስፈራሪያ ከስልኳም ያለፈ ነበር። ሌሎች የማህበረሰቡን አባላት ለመተዋወቅ በመፈለጓ ሌዝቢያን ነኝ ካለቻት ሴት ጋር በማውራት ላይ ነበረች።

ከአዲስ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ሴት ጋር ልትገናኝ እንደሆነ በማሰብ የተደሰተችው ሰላም አጠራጣሪ ነገሮች እያየችም ማዋራቷን አላቆመችም። ሴቷ በተደጋጋሚ ታሪኳን ከመቀያየሯ በተጨማሪ ሁኔታዋ አስተማማኝ አልነበረም። ሰላም ይህንን በነገረቻት ወቅት ስለፈራች እንደሆነ በማሳወቅ ቀለል አርጋ አሳለፈችው። ሰላም ጥርጣሬዋ እንዳለ ማውራቷን ቀጠለች።

"ብዙ ያጠራጠሩኝ ነገሮች ነበሩ ግን ጥሩ ንግግር እናደርግ ስለነበር እንዲቆም አልፈለኩም" ትላለች። "አልዋሸሽኝም አይደል ብዬ ራሱ ጠይቄያታለሁ።"

ሰላም በተቀጣጠሩበት ቦታ በሰአቷ ስትደርስ እያዋራቻት የነበረችው

**"እንዴት ፎቶዬን እንዳገኘው አላውቅም፤ ቴሌግራሜ ስለራሴ ያለውን መረጃ እንዳያሳይ አድርጌው ነበር። ..."**

**ሳባ**

## “ብዙ ያጠራጠሩኝ ነገሮች ነበሩ ግን ጥሩ ንግግር እናደርግ ስለነበር እንዲቆም አልፈለኩም።”

**ሰላም**

ሴት እውነትም ሴት እንደነበረች አረጋገጠች። ግን የመጣችው ከወንድ ጋር ነበር።

ፈጠን ብላ በማሰብ ሰላም ሌላዋን ሴት ካትፊሽ እያረገቻት እንደነበር አስመሰለች፤ ይህም ከአደጋ ጠብቋታል። የሚመረጥ ባይሆንም በሰአቱ ራሷን ለመጠበቅ አስፈላጊ ነበር፤ እንገናኝ ብላ የጠየቀችው ራሷ መሆኗም እንድትታመን ረዳት።

ታሪኳ ብዙ ውጣ ውረዶች አሳልፎ በመጨረሻ ግን ከሴቷ ጋር አብራ በመሆን ተጠናቋል። ሴቷ ከተመሳሳይ ጾታ ጋር መሆን ብትፈልግም ካትፊሽ እደረጋለሁ ብላ ፈርታ ነበር። ሰላም ከዚህ ችግር በማምለጧ እድለኛ ነች፤ ከልምዱም ብዙ ተምራለች። ይሁንና የተገናኙበት መንገድ ልክ ባለመሆኑ ከዚች ሴት ጋር ትርጉም ያለው የፍቅር ህይወት እንድትመራ አላስቻለም በመሆኑም ተለያዩ።

ሰላም የፍቅር ግንኙነቶችን በተመለከተ የምታደርገው ጥንቃቄ ከጥቁር ሰው ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ ጥቁር ጥንቃቄዋ በኦንላይን ግንኙነት ላይ ያላትን እምነት እንድታጣ አድርጓታል።

ጥቁር ሰው፡ እምነትን ማጣት

ሌዝቢያን የሆነችው ጥቁር ሰው ያሳለፈችው አጋጣሚ አካውንቷን ሙሉ ለሙሉ እንድታጠፋ አድርጓታል። ፌስቡክ ላይ ሰው ማዋራት ከጀመረች በኋላ ፎቶ እንድትልክ ተጠየቀች። መጀመሪያ እንዲልኩላት ስትጠይቅ የደበዘዘ ማይታይ ፎቶ ላኩላት። ጥቁርሰው ካትፊሽ እየተደረገች እንደሆነ ያወቀችው በሌላ አፐ ደውላ ወንድ ሲያነሳው ነው

“ለሁለት ወር ያህል ፌስቡክ ላይ አልነበርኩም። በቀላሉ የማልፈው ነገር አልነበረም በጣም ተናድጄ ነበር።” ስትል ታስታውሳለች።

ከቆይታ በኋላ ፌስቡክ ለኩዊር ማህበረሰቡ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት መጠቀም ጀመረች። ይሁን መጀመሪያ ከሌሎች ጓደኞቿ ማረጋገጫ ሳታገኝ ማንንም ሰው ላላማናገር ወስና ነበር።

እምነቷ በመናዱ አሁን ላይ ሰውን ሙሉ በሙሉ ማመን ይከብዳታል።  ጥቁር ሰው ኦንላይን የምታገኘውን ሰው ከባድ ሆኖ ብታገኘውም ቦኒ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ካለ ሰው ነው ክህደት የደረሰባት ይህም ከማንጠብቀው ቦታ ጭምር አደጋ ሊያጋጥመን እንደሚችል ማሳያ ነው።

ቦኒ፡ የማህበረሰብ ሀይል

አንዳንዴ በዙሪያችን የሚገኙት ሰዎች ኩዊር መሆናቸውም ደህንነታችን ላያስጠብቅ ይችላል። ቦኒ የጾታ መገለጫ የማትጠቀም ሲሆን አንቺ መባልን ትመርጣለች። የተጋለጠችው ደግሞ በሌላ ኩዊር የሆነ ሰው ነበር።

ቦኒ ካትፊሽ ከመደረግ ጋር ያለውን ችግር ስለምትረዳ የግል መረጃን ማጋራት እና ተለዋዋጭ የሆኑ ታሪኮችን ስትሰማ መጠራጠር፤ የሰውን ማንነት ለማረጋገጥ ለጓደኞቿ እና ሌሎች የማህበረሰብ አባላት ጥያቄ ማቅረብ፤ ያ ሰው ስለኩዊር ያለው እውቀት ምን ያህል እንደሆነ ማጣራት እና ቀልቧን ማመን ልምዷ ነው።  በመሆኑም ካትፊሽ እደረጋለሁ ብላ አስባ አታውቅም።

ይሁንና ማህረሰቡ ውስጥ ያለ ሰው ያጋልጠኛል ብላ በጭራሽ አልጠበቀችም፤ ይህም በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ጥላቻ በተሞላችው ኢትዮጵያ መኖርን ይበልጥ ከባድ እንዲሆንና እምነት እንድታጣ አድርጓታል።

“ያ ነገር ከደረሰብኝ በኃላ ለኩዊር ማህበረሰቡ ያለኝ እምነት ተንዶ ነበር ግን ከተጋለጥኩ በኋላ ስሜን እንኳን የማያውቁት ሰዎች ነበሩ ሊረዱኝ ከጎኔ የተገኙት።” ስትል ትናገራለች። “ህመሜን እንደሚረዱት

## “ለሁለት ወር ያህል ፌስቡክ ላይ አልነበርኩም።”

**ጥቁር ሰው**

ገባኝ። ሊረዱኝ የመጡት ስለሚያውቁኝ ሳይሆን ይህ ነገ በነሱም ላይ ሊከሰት የሚችል ነገር እንደሆነ በማሰብ ነው።"

በመሆኑም በኲዊር ሰው በመጋለጥ ያጣችው እምነት በማህበረሰቡ ሊመለስላት ችሏል።

የቦኒ ልምድ እምነት እንዴት ጥንቃቄ የሚፈልግ ነገር እንደሆነ ያሳየናል። ጆይ በበኩሏ በኲዊር ማህበረሰብ ውስጥ የፍቅር ግንኙነቶችን ማስኬድ ከባድ ስለመሆኑ ትነግረናለች።

ጆይ፡ ሰላማችንን መጠበቅ መማር

ወንዳወንድ መገለጫ እንዳላት ሌዝቢያን ጆይ ኪዉር ሰዎችን መተዋወቅ እና በአካል መገናኘት ያስደስታታል። ይህም መርጣ ቤተሰብ ካረገቻቸው ሰዎች ጋር ከሌሎች ጋር ሊኖራት የማይችለውን አይነት ግንኙነት እንድትፈጥር ይረዳታል።


ይሁንና ኲዊር መሆን ብቻ በቂ እንዳልሆነ ተምራለች። "ብዙ ራሳቸውን ኲዊር የሚሉ ግን ማንነታቸውን ያልተቀበሉ ሰዎች አሉ" ትላለች። ሰዎች ራሳቸው ወደሚቀበሉበት መንገድ መምራት አስፈላጊ ነው ብላ ታስብ ነበር ይሁንና አሁን ላይ ጉልበቷን እዛ ላይ ማባከን እንዳማያስፈልግ ተረድታለች።

ከጆይ ጓደኞች አንዷ የማህበረሰቡ አባል በሆነ ሰው ለአደጋ ተጋልጣ ነበር። ይህች ጓደኛዋ ክርስቲያንነትን በድጋሚ ተቀብያለው ባለ ጓደኛዋ በተደጋጋሚ ሀጥያት ውስጥ መኖር እንድታቆም እና ፈጣሪን ወደህይወቷ እንድታስገባ ይነገራት ነበር።

ጆይ ጓደኛዋ በዚህ ሰው እንዳይጋለጥ ትፈራ ነበር። በዚህም የተነሳ ያላት ግንኙነት የተመጠነ መሆን እንዳለበት ተረዳች።

**"ስለዚህ አትገናኙ ማለት ይከብዳል ነገር ግን ስንገናኝ ሰርክሉን ትንሽ አድርገን በጣም ደህንነት የሚሰማን እንደ መኖርያ ቤቶች ወይም ደግሞ በጣም ከእይታ የወጡ እና እርግጠኛ የሆንባቸው ቦታዎች ላይ መሰባሰብ ይሻላል።"**

**ጆይ**



## “ያ ነገር ከደረሰብኝ በኋላ ለኩዊር ማህበረሰቡ ያለኝ እምነት ተንዶ ነበር።”

**ቦኒ**

“አሁን አሁን የዚህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ አልገኝም። ኩዊር ሰዎችን አላገኝም ማለት ሊሆን ይችላል ግን ደግሞ ራሳቸውን ካልተቀበሉ እና ህይወቴን ችግር ውስጥ ሊከቱ ከሚችሉ ሰዎችም ርቄያለሁ ማለት ነው።” ስትል ትናገራለች።

ጆይ ሰላሟን እና የአእምሮ ጤናዋን መጠበቅ ላይ ስታተኩር የብሉ ታሪክ ደግሞ አደጋ እንዳለው እያወቁም ግንኙነቶችን መፈለግ ስላለው የስሜታ መቃወስ ታወጋናለች።

ብሉ፡ ተስፋ እና ጽናት

ብሉ ፌስቡክ በፎቶዋና የግል መረጃዋ ካሁን አሁን ተሞላ ብላ ስትጠብቅ ለቀናት መተኛት አልቻለችም ነበር። ሌዝቢያን መስሎ በቀረባት ወንድ ካትፊሽ ተደርጋ ነበር፤ለሱ ኩዊር ኢትዮጵያዊ ሴቶችን ካትፊሽ ማድረግ እንደስፖርት እና መዝናኛ ነበር። ይህንን በግልጽ አሳውቋታል።

ለኩዊር ማህበረሰቡ አዲስ እንደመሆኗ ከሌሎች ሌዝቢያን ሴቶች ጋር ለመተዋወቅ ካላት ጉጉት የተነሳ ካትፊሽ ልትደረግ ችላለች፡ ጥሩ ያልሆነ ስሜት እየተሰማትም ማዋራት አላቆመችም ነበር ይህንንም ያደረገችው እስካዋራሁት ድረስ አያጋልጠኝም በሚል እሳቤ ነው።



በርግጥ አላጋለጣትም ግን ፍርሀት እና ጭንቀቱ የአእምሮ ጤናዋ ላይ ተጽእኖ ፈጥሯል። ማንነቷን አጋልጦ የቤተሰቧን ፍቅር እና የገንዘብ ድጋፍ ያሳጣኛል ብላ ፈርታ ነበር።

ከሶስት አመታት በኋላ ለድሮዋ እሷ አሁንም ሀዘን ይሰማታል። ባትጋለጥም የተጨነቀችውን ጭንቀት ትጸጸትበታለች። አሁን ባለትዳር ስትሆን ከባለቤቷ ጋር በመተሳሰብ ይኖራሉ።

“የምንኖረው ከቤተሰባችን ጋር ነው፤ በራሳችን አንተማመንም፤ በዛ ላይ ስራ የለንም። አሁን ግን ነጻነት አለን ምንም ቢፈጠር ከባለቤቴ ጋር አንዳችን ለአንዳችን አለን፤ እኔም እደግፋታለሁ እሷም እንደምትደግፈኝ ተስፋ አለኝ።” ትላለች። “ያሳለፍኩት ነገር በጣም ጠንካራ እንድሆን አርጎኛል፤ ሰው እንዳለኝ እንዳውቅ እና የራሴንም ጥንካሬ እንድረዳ አግዞኛል።”

ብሉ ስላሳለፈችው አጋጣሚ ያላት እይታ ጽናትን በሰፊው የሚያመላክት እና የኢትዮጵያ ኩዊር ማህበረሰብ በአብሮነት ያለውን ጠንካራነት የሚያስታውሰን ነው።

መዝጊያ፡ ብሩህ ወደፊትን መገንባት

በሳባ፤ ሰላም፤ ጥቁር ሰው፤ ቦኒ፤ ጆይ እና ብሉ የተጋሩት ታሪኮች በኢትዮጵያ የሚገኙ ኩዊር ሰዎች የሚያጋጥማቸውን አደጋ የሚያሳይ

ነው። እያንዳንዱ ታሪክ ካትፊሽ መደረግ፤ መጋለጥ እና የስም መጥፋት የተለመዱ መሆናቸውን ይነግረናል። ይህም የፍርሀት ስሜትን በመፍጠር እውነተኛ ግንኙነቶችን ለማዳበር ከባድ እንዲሆን ያደርገዋል።

ይሁንና በነዚህ ችግሮች ውስጥም የማይናድ ጽናት አለ። የማህረሰቡ መደጋገፍ አስፈላጊ እና ሰዎች በሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንዲረዳዱ የሚያስችል ነው። የቦኒ በኩዊር ሰው መጋለጥ በማህረሰቡ ውስጥ ያለውን ክፍተት የሚያሳይ ቢሆንም ይኸው ማህበረሰብ በአብሮነት ለመደጋፍ ዝግጁ እንደነበርም አስታውሶናል።

ጆይ ሰላሟን ለመጠበቅ ያላትን ቁርጠኝነት ስናይ ሁሉም ግንኙነቶች ትክክለኛ ላይሆኑ እንደሚችሉ እና ሰዎችን በጥንቃቄ መምረጥ እንዳለብን እንረዳለን። ብሉ ከፍርሀት ወደ ፅናት ያደረገችው ጉዞ ስለግል እድገት የሚያሳውቀው ሲሆን በከባድ ጊዜያት እንኳን ሁሌም ለመዳን እና ለጥንካሬ ተስፋ እንዳለ ማረጋገጫ ነው።

እነዚህ ታሪኮች በኢትዮጵያ ለሚገኙ የኩዊር ማህበረሰብ አባላት መንገዱ ከአደጋ የነጻ እንዳልሆነ ቢያስታውሱንም የማህበረሰብ ሀይል ብሩህ እና የሚቀበል ነገን መገንባት እንደሚቻል ማሳያ ነው። በተጋላጭነት ውስጥ ጥንካሬ አለ፡ በአብሮነት ዝም ሊያስብላቸው የሚፈልገውን ህብረተሰብ በተስፋ ብሩህ ለማድረግ አቅም አላቸው።

**“ያሳለፍኩት ነገር በጣም ጠንካራ እንድሆን አርጎኛል፤ ሰው እንዳለኝ እንዳውቅ እና የራሴንም ጥንካሬ እንድረዳ አግዞኛል።”**

**ብሉ**

# ... በከባድ ጊዜያት እንኳን ሁሌም ለመዳን እና ለጥንካሬ ተስፋ አለ



## - ኤስ -

በደንብ ካትፊሽ ተደርጌያለሁ። ማንነቴን፣ የት እንደምኖር እና የቴሌግራም አካውንቴን ካትፊሽ አድርገው የደረሱብኝ ሶስት ሰዎች ነበሩ። ስለ አንደኛው ልንገራችሁ። ፌስቡክ ላይ የከፈትኩት ፌክ አካውንት ነበር። ልጁን ምንም ልለየው አልቻልኩም። እኔ በኢንተርኔት ለመገናኘት አዲስ ነበርኩ እና ኩዊር ሰዎች እንዴት እንደሚግባቡ እና ምን አይነት ወሬ እንደሚያወሩ አላውቅም ነበር። ብቻ ወንድ እንደሆነ ምንም መጠርጠር አልቻልኩም። ትክክለኛ ስሜ ማን እንደሆነ እና የት እንደምኖር አያውቅም። እንዴት እንደደረሰበት አላውቅም፤ የሆነ ቀን ምን እንዳለኝ በእርግጠኝነት ባላስታውሰውም ሳስበው ራቁትሽን ፎቶ ላኪልኝ ብሎኝ ነው የሚሆነው። እንደዚህ አይነት ነገር እኔ አላደርግም፤ ወደፊትም አላደርግም ስለው ይቆጭሻል እያለ ማስፈራራት ጀመረ። አውቅሻለሁ "አትሳፈጪኝ" አለኝ እና ትክክለኛ የፌስቡክ አካውንቴን ስክሪንሾት አድርጎ ላከልኝ። ካላወራሽኝ አጋልጥሻለሁ እና ፖስታ አደርግሻለሁ ብሎ ተጨቃጨቀ። ከዛ በኋላ አካውንቱን ዘጋሁት።

# የኦንላይን ደህንነት መጠበቂያ ጠቃሚ ምክሮች

## 1 በዋነኛ አካውንትዎት የሚያጋሩትን መረጃ ይጠንቀቁ

- በይፋዊ ፕሮፋይሎች ላይ የተጋራውን የግል መረጃ ይገድቡ
- ማን የእርስዎን ፖስቶች እና የጓደኛ ዝርዝሮች ማየት እንደሚችል ለመገደብ የግላዊነት ቅንብሮችን (privacy setting) ያስውንም የኩዊር ድጋፊ ይዘትን ለማጋራት አይጠቀሙ ወይም በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ካሉ ግልጽ የኩዊር አካውንቶች ጋር ለመገናኘት አይጠቀሙ
- ዋነኛ የማህበራዊ ሚዲያ አካውንቶ ላይ የወሲባዊ ወይንም የጾታዊ ዝንባሌ መለያዎችን (ለምሳሌ ቀስተ ዳመና ወይም ተመራጭ ተውላጠ ስሞችን ወዘተ) ከመዘርዘር ይቆጠቡተካክሉ
- ዋነኛ የማህበራዊ ሚዲያ አካውንቶ ላይ ማንኛ

## 2 የኩዊር የማህበራዊ ሚዲያ አካውንትዎ ይክፈቱ

- ማንነትዎን የማይገልጹ ተለዋጭ ስሞችን በመጠቀም ከወሲባዊ ዝንባሌዎ ወይንም ከጾታዊ ማንነትዎ ጋር የሚገናኙ ስራዎችን ለመስራት የሚሆን የኩዊር (ፌክ) አካውንት ይክፈቱ
- የኩዊር (ፌክ) አካውንትዎን ከዋናው አካውትዎ እና ከዋነኛው ኢሜል አድራሻዎት ጋር አያገናኙት
- ያሉበትን ቦታ ከፖስትዎ ወይም ከፎቶዎ ጋር አብሮ ከመለጠፍ ይቆጠቡ
- በኩዊር (ፌክ) አካውንትዎ ከጓደኞችዎ ጋር በዋነኛ መለያዎቻቸው ለመነጋገር (ለምሳሌ በፖስት ላይ ኮመንት መስጠት ወዘተ) አይጠቀሙ ምክንያቱም እነሱንም አደጋ ላይ ይጥላል
- የማህበራዊ ሚዲያ ጓደኞቹትን ወይም ፎሎወሮችን በመደበኛነት ይገምግሙ እና አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ያስወግዱ

## 3 በኩዊር የማህበራዊ ሚዲያ አካውንትዎት የሚያጋሩትን መረጃ ይጠንቀቁ

- በዚህ መለያ ላይ የትኛውንም ሊለይ የሚችል የግል መረጃ አይለጥፉ ወይም በሜሴጅ አይላኩ (ለምሳሌ የእርስዎ ትክክለኛ ስም ወይም የታወቁ የቤት ስሞች፣ ሙሉ ወይም ከፊል የእራስዎ ምስሎች ፣ ሊለዩ የግል ዕቃዎችዎ እና ብዙ ጊዜ የሚለብሱትን ልብስ ፣ንቅሳት / ጠባሳዎች / መበሳት ፣ የሚዘወተሩባቸው ቦታዎች ፎቶዎች ወዘተ)
- አካውንትዎን ወደ የግል ያቀናብሩ (privacy setting) እና የሚምጣሎትን የፍሬንድ ሪኩዌስት በጥንቃቄ ይገምግሙ። ከሚያውቁት ሰው ብቻ የመጣውን ይቀበሉ። አለዚያም ፖስቶቻቸውን በጥንቃቄ ይመርምሩ ፣ የጓደኞቻቸውን ዝርዝር ይመልከቱ እና ከሌሎች ታማኝ የኩዊር ጓደኞች ጋር ያረጋግጡ

## 4 ስለ የማህበራዊ ሚዲያው ፖሊሲዎች መረጃ ያግኙ

- የሚጠቀሙባቸውን የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ህግጋት እና መመሪያዎችን ይረዱ
- ትንኮሳ ወይም ማስፈራሪያ ሲያጋጥም እራስዎን ለመጠበቅ ሪፖርት ማድረጊያ መንገዶች ጋር ይተዋወቁ
- ለደህንነትዎ አስፈላጊ ከሆነ አካውንትዎትን እንዴት በፍጥነት ማጥፋት ወይም መሰረዝ እንደሚችሉ ይወቁ



## - ቢ -

ካትፊሽ ተደርጌ አላውቅም። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ቅድመ ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ። እንደዚህ አይነት ሰው እንዳታገኙ እያሉ ይጽፋሉ፤ ክፉ ነገር ሲያደርጉ የተደረሰባቸዉ ሰዎች ማለት ነው። እንደ እድል ሆኖ ያንን ያንንም ከማየት ይመስለኛል ትንሽ እፈራለሁ፤ ዴቲንግ ላይ ከማግኘቴ በፊት በጣም ለመመርመርም እሞክራለሁ። እንደ እድል ሆኖ በዴቲንግ ሳይቶች ወይም በሶሻል ሚዲያ ተሸውጄ ያጋጠመኝ ነገር የለም።

# በአካል ከሰዎች ጋር ለመገናኘት ጠቃሚ ምክሮች

1

## ከመገናኘትዎ በፊት ማንነታቸውን ያረጋግጡ

- የጋራ ጓደኞችን ይፈልጉ ወይም የማህበራዊ ሚዲያ ፖስታቸውን ለትክክለኛነት ያረጋግጡ። ኩዊር ጓደኞችዎ እያናገሩት ያለውን አካዉንት ባለበት ያውቁ እንደሆነ ያጣሩ
- ማንነታቸውን ለማረጋገጥ በአካል ከመገናኘትዎ በፊት የስልክ ጥሪ እና የቪዲዮ ውይይት ያዘጋጁ

2

## የህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎችን ይምረጡ

- ደህንነትዎን ለማረጋገጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመገናኘት ጥሩ ብርሃን ያላቸውን የህዝብ ቦታዎች (እንደ ካፌዎች ወይም መናፈሻዎች) ይምረጡ። ለመጀመሪያ ስብሰባዎች የተገለሉ ቦታዎችን ወይም የግል ቤቶችን ያስወግዱ።
- ከማን ጋር ሲገናኙ እንዳሉ፣ የትና መቼንም ጨምሮ ዕቅዶችዎን ለጓደኛዎት ያጋሩ
- የማምለጫ መንገድ ያቅዱ ወይም ምቾት ካልተሰማዎት ጥሎ ለመሄድ መንገድ ይኑርዎት

3

## የራስዎን መጓጓዣ ይጠቀሙ

- ሁኔታዎን ለመቆጣጠር እንዲመቾት እና የሚያገኙት ሰው ላይ መተማመን እንዳያስፈልግዎት  ከተቻለ ወደ ወደመገናኛው ቦታ ሲሄዱ እና ሲመለሱ የእራስዎን መጓጓዣ የጠቀሙ
- የስልክዎ ባትሪ ሙሉ ያድርጉ እና የመጓጓዣ  አማራጮችን (እንደ ራይድ/ፈረስ ወይንም ታክሲ ያዘጋጁ

4

## ስሜቶን ይመኑ

- ለአካባቢዎ እና በአቅራቢያዎ ላሉት ግለሰቦች ንቁ ይሁኑ። ስለ ሰዎች ወይም ሁኔታዎች ያለዎትን ስሜት ይመኑ። የሆነ ነገር ልክ ካልመሰሎት ግንኙነቱን ለማቋረጥ ወይም ጥሎ ለመሄድ አያመንቱ
- ከአልኮል ወይም ከአደገኛ ዕጾች ጋር ጥንቃቄ ያድርጉ፣ ምክንያቱም ፍርድዎን ሊያበላሹ ይችላሉ



## - ቲኤስ -

ሜሪ ይባል ነበር እና እኔም ሴት መስላኝ ማውራት ጀመርኩኝ። ማውራት ከጀመርንበት ቀን ጀምሮ ፎቶሽን ካላሳየሽኝ ብላ ስትጨቀጭቀኝ “ተረጋጊ በደንብ ስንተዋወቅ ታይኛለሽ” ስላት እምቢ አሻፈረኝ አለች። እኔም መጠርጠር ጀመርኩኝ። “እሺ ያንቺን ፎቶ አሳይኝ እና እኔም የኔን አሳይሻለሁ” አልኳት። የላከችልኝ ፎቶ ግን የደበዘዘዘ እና በደንብ የማይታይ ስለነበረ ጭራሽ የበለጠ ተጠራጠርኩኝ። ይሄማ ወንድ ነው ብዬ አሰብኩ እና ሜሴንጀር ላይ ደወልኩኝ። አይነሳም በጣም በተደጋጋሚ ደወልኩኝ፤ ልታነሳ አልፈቀደችም። መጨረሻ ላይ “በቃ ብሎክ ላደርግሽ ነው ወይስ ወንድ ስለሆንክ ነው ነህ ማውራት ያልፈለከው” አለኩት። ዝም ሲለኝ “አውቄዋለሁ” ስለው አዎ ወንድ ነኝ አለኝ። ከዛ እራሱ ሜሴንጀር ላይ መልሶ ደወለ እኔም አንስቼ ሄሎ አልኩት፤ እሱም ሄሎ ሲለኝ ወንድ እንደሆነ አረጋገጥኩኝ። ከዛ ብሎክ አደረግሁት ለጓደኞቼም ዩዘርኔም እና ፎቶውን አድርጌ ይሄ አካውንት ወንድ ነው ተጠንቀቁ ብዬ ነገርኳቸው። ለካ ሌሎች ኩዊር ሰዎች እያዋራ ነበር ሁሉም አመስግነውኝ ብሎክ አደረጉት።

# የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ደህንነት መጠበቂያ ጠቃሚ ምክሮች

1

## የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችዎን ደህንነት ይጠብቁ

- ለስልክዎ ጠንካራ፣ ልዩ የሆኑ የይለፍ ቃሎችን ይጠቀሙ እና በሚቻልበት ጊዜ ለመለያዎችዎ ባለ ሁለት ደረጃ ማረጋገጫን (two-factor authentication) ይጠቀሙ
- መሣሪያዎችዎን በቅርብ ጊዜ በወጡ የደህንነት ጥገናዎችን ያዘምኑ

2

## ደህንነቱ የተጠበቀ የግንኙነት አፖችን ይጠቀሙ

- ከጫፍ እስከ ጫፍ ምስጠራ የሚያቀርቡ (end-to-end encryption) መተግበሪያዎችን ይምረጡ (ለምሳሌ፡ ሲግናል፣ ቴሌግራም)
- በመገናኛ አፖችዎ ላይ የይለፍ ቃል ቁልፎችን ያድርጉ (የሚመረጠው ባዮሜትሪክ አይደለም)
- ቀጥታ የጽሁፍ መልእክት እና ጥሪ ከመንግስት ክትትል ደህና አይደሉም

3

## የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችዎን ንጽህና ይጠብቁ

- የቻት ሂስትሪዎን፣ ፎቶዎችን፣ አፕዎችን፣ ሰርች ሂስትሪዎችን የኩዊር ይዘት በየጊዜው የፈትሹ እናም ያጽዱ
- የኩዊር የማህበራዊ ሚዲያ አካውንትዎን ሎግ አውት ያድርጉ
- ከኩዊርነት ጋር የተገናኙ ምስሎችን ፎቶዎችን ፣ ጽሑፎችን ፣ ቴክስቶችን ወዘተ ኦንላይን (cloud) ያስቀምጡ እንጂ በስልክዎ ላይ አይሁን
- ካስፈለገዎት የትኞቹን የኩዊር ወይም ሚስጥራዊነት ያለው ውሂብ (የተወሰኑ ፎቶዎች፣ ቻቶች፣ የኩዊር ዴቲንግ አፖች ወዘተ) በፍጥነት መደለት እንዳለቦት ይወቁ

HER

Grindr

4

## ስም-አልባ አሰሳ (ANONYMOUS BROWSING)

- ከኩዊር ጋር ለተያያዙ ፍለጋዎች ለግላዊነት ቅድሚያ የሚሰጡ አፖችን (ለምሳሌ፡ ቶር፣ ዳክ ዳክ ጎ) ይጠቀሙ
- አንዳንድ ዌብሳይቶች እንቅስቃሴዎን ሊመዘግቡ እንደሚችሉ ይወቁ፣ ስለዚህ ማንነትን የማያሳውቅ (incognito) ወይም የግል የአሰሳ ሁነታን (private browsing) ይጠቀሙ።

# ከውስጥ መጋለጥ

ደህንነቴ የተናጋው ከማህበረሰባችን ውስጥ ከሆነ ሰው ቢሆንም ሁሉም የማህበረሰባችን አባል ሁሉ መጥፎ ነው ማለት አይደለም





የኔን መሞት እንደሚፈልጉ ነገሩኝ። እንደዚህ አይነት ማንነት ይዤ መኖር እንደሌለብኝና መሞት እንደሚገባኝ በተደጋጋሚ ነገሩኝ። እሱ አልበቃ ሲላቸው ደግሞ ጨመሩልኝ፤ ጭራሽ አከራዮቼ ሊገድሉኝ ይገባ እንደነበረ ነገሩኝ። የሰፈር ሰው ወሬ ማለቂያ አልነበረውም። ያው የስድብ ናዳ፣ የድብደባ ሙከራ፣ የመንገድ መዘጋት ሙከራ እና በሰላም እንዳልራመድ በምሄድበት በማልፍበት መንገድ ትንኮሳ በሽ ነበር።

የሚያሳዝነው ነገር ለዚህ ሁሉ አበሳ የተዳረኩት የእኔ በምላቸው የኩዊር ማህበረሰብ አባላት ነው። ተከብሬ የሥራ ሰው በተባልኩበት ሰፈር በአንድ ጊዜ ጠላተ ብዙ ሆኜ አይኔን ለአፈር የሚመኝልኝ በዛ። በጥድፊያ ሰፈር ለቅቄ ለመሄድ ተዘጋጀሁ። በችኮላ እቃዬን እንኳን በቅጡ ሳላዘጋጅ እንደሌባ ስንት አመት በኪራይ ከኖርኩበት ቤት እና ሰፈር በሰቀቀን እና በጥድፊያ በአሳቻ ሰአት ለቅቄ ወጣሁ።

የኩዊር ማህበረሰባችን አካል የሆነው ሰው የእኔን እና የሌሎችንን ኩዊርነት እዚህ ግባ በማይባል ተልካሻ ምክንያት ያለፍቃዳችን ኩዊርነታችንን ገሃድ አድርጎ አወጣው። በእርግጥ ይህ ሰው እና ሌሎች እሱን የመሰሉ ሰዎች ይህንን የሚያደርጉት ለራሳቸው ካላቸው የተንሻፈፈና የቀጨጨ ግንዛቤ በመነሳት ነው። ለሌሎች የኮሚኒቲያችን አባላቶች ያላቸው ጥላቻ ራስን ከመጥላት እና ራስን ካለመቀበል የሚመነጭ እንዲሁም የሌሎችን ውድቀት እና የሌሎችን መጥፋት ከሚመኙ ሰዎች ነው። እራሳቸውን ካለመቀበላቸው የተነሳ ያመጡት ጣጣ ግን ለእኔ ተረፈኝ።

ከዛን ጊዜ በኋላ ጀምሮ ኃይለኛ የፍርሐት ስሜት ይሰማኛል። በራስ የመተማመን ስሜቴ ቀንሷል። በማንኛውም ሰዓት አደጋ ሊደርስብኝ እንደሚችል ነው የማስበው። በማንኛውም ሰዓት አደጋ ሊገጥመኝ እና ጥቃት ሊሰነዘርብኝ  እንደሚችል ይሰማኛል። ምንም ዓይነት በራስ የመተማመን ስሜት አይሰማኝም። ብቻዬንም ሆኜ ይሁን አልፎ አልፎም የህዝብ ቦታዎች ላይ ስንቀሳቀስ ከፍተኛ ስጋት እና የምቾት አለመሰማት ስሜት ይሰማኛል። ሌሊት በህልሜ ሳይቀር የማልመው ጥቃቶች ሲደርስብኝ ነው። ስጋት ሁሌም የማይለቀኝ እና ከዛ አንጻር አይምሮዬ በፍጹም ሊቀበለው ያልቻለው አደጋ (trauma) ነው የሆነብኝ።

በቤተሰብ እና በጓደኞቼ እንዲሁም በስራ ቦታዬ ላይ ያመጣው ተፅኖም ቀላል አይባልም። ፍርሃትና በራስ መተማመን ማጣት ስላለብኝ ከስጋቴ የተነሳ ማንነቴን ከማያውቁ ሰዎች ጭምር ጠፍቻለሁ። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ማንነቴን ቢያውቁ ጥቃት ያደርሱብኛል፤ ህይወቴ ላይ አደጋ ይደርሳል ብዬ ስለማስብ ከአብዛኛው ማህበራዊ ህይወት እራሴን አግያለሁ። ጥቃት ከተፈጸመብኝ በኋላ ከሰው ጋር ከመሆን ይልቅ ብቻዬን ማሳለፍ ነው የሚያስደስተኝ። እንደውም ግዴታ ካልሆነብኝ በስተቀር ኩዊር ካልሆኑ ሰዎች ጋር ምንም ያህል ጊዜ ማሳለፍ አልፈልግም። ይህም ደግሞ በራስ መተማመን ስለማይሰማኝና ማንነቴን ቢያውቁ ከጥላቻቸው የተነሳ እስከ ግድያ እና ከፍተኛ የሆነ ህይወትን አደጋ ውስጥ የሚከት እርምጃ ከመውሰድ የሚቆጠብ ሰው እንደሌለ ስለሚሰማኝ ነው። ለዚህም መፍትሄ ራሴን ማግለል እንድሆነ ተቀብያለሁ።

ይህ ሀገር በነፃናት ለመኖር የተመቸ አይደለም። ማንነቴን ካጋለጡኝ በኋላ የተማርኩት ትምህርት ቢኖር ሰዎችን ምንም ያህል ላምናቸው ብችልም ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ የተነሳ በቤቴ ውስጥ ብቻዬን በምሆንበት ሰዓት እንኳን ከአደጋ ነፃ እንዳልሆንኩኝ ነው። የተዘጋ በር እና ማንም በማያየኝ ሁኔታ ውስጥ እንኳን ራሴን ለመሆን በጣም ነው የምፈራው። ብቻዬን ሆኜ ራሱ ወደ ግራ እና ወደቀኝ ልዞር እችላለሁ፤ ብቻዬን እንደሆንኩኝ እና በሬ እንደተቆለፈ እንኳን እያወኩኝ ያን ያህል መተማመን የለኝም። ራሴን የምገልጽበት ምንም ዓይነት ቦታ አጥቻለሁ ምክንያቱም በማንኛውም ሰዓት ችግር እንደሚገጥመኝ ነው የማስበው።

ሊዘነጋ የማይገባው ነገር ይህንን ሁሉ ስል ደህንነቴ የተናጋው ከማህበረሰባችን ውስጥ ከሆነ ሰው ቢሆንም ሁሉም የማህበረሰባችን አባል ሁሉ መጥፎ ነው ማለት


አይደለም። እኔ ከደረሰብኝ ችግር እንድወጣ የረዱኝ፣ የመከሩኝ፣ በገንዘብም ይሁን በተለያየ ነገር የረዱኝ ሰዎች በኮሚኒቲያችን ውስጥ ያሉ እና ለኮሚኒቲው የሚሰሩ ሰዎች አሉ። ኮሚኒቲ ውስጥ ያለ ሁሉም ሰው አንድ አይደለም፤ ሁሉም ሰው ደግሞ ሰውን ለመጉዳት የሚንቀሳቀስ አይደለም። እንደዚህ አይነት ችግር ስለገጠመኝ በጣም አዝኛለሁ ግን በዛው ልክም ደግሞ ካለሁበት ችግር እንድወጣ በጣም ያገዙኝ ሰዎች አሉ። ስለዚህ ይህ የሚያሳየው ሰዎችን መርጦ የመቅረብ ጉዳይ ነው እንጂ ሁሉም ኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ ያለ ሰው የማይታመን ነው ማለት እንዳልሆነ ነው።


በእርግጥ በተለይ ደግሞ እንደዚህ አይነት ችግር ውስጥ ሲገባ የምናስበው በጣም ጨለምተኝነት እና ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር ነው። ስለሆነም ከሰዎች ጋር መነጋገር እና መመካከር እንደሚያስፈልግ ማወቅ አለብን። ከመመካከርም ባለፈ ያለብንን ችግር የእውነት እንደሚረዱን ለምናምናቸው ሰዎች በግልጽ መናገር አለብን። ተናግረንም ምን አይነት መፍትሄ እንደሚያስፈልገን እና ያለብን ክፍተቶች የኢኮኖሚም ይሁን የእውቀት በግልጽ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያለ ሀፍረት እና የበታችነት ስሜትም ሳይሰማን እርዳታዎችን በመጠየቅ ወደ መፍትሄ ለመጠጋት መሞከር የተሻለ ነው።

ያው ቢሆን ቢሆን ማንነታችን ያለእራሳችን ፍቃድ እንዳይጋለጥ መጀመሪያው ጥንቃቄ መውሰድ ግን አንዴ ከሆነ ወዲህ በተቻለ መጠን ከገባንበት ችግር ውስጥ እንዴት ነው መውጣት የምንችለው የሚለው ላይ ትኩረት ማድረግ ይበጃል። ይህን ማድረግ እንዴት ከባድ እንደሆነ ግን ውስጡ ሆኜ እያየሁት ነው።

> በችኮላ እቃዬን እንኳን በቅጡ ሳላዘጋጅ እንደሌባ ስንት አመት በኪራይ ከኖርኩበት ቤት እና ሰፈር በሰቀቀን እና በጥድፊያ በአሳቻ ሰአት ለቅቄ ወጣሁ።

# ካትፊሽ፡ የአጭር ርቀት ሩጫ





እንደ ብዙ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳሉ ኲዊር እህቶቼ እና ወንድሞቼ ማንነቴን እንዳወኩኝ ሩጫዬን ወደ ጉግልና ወደ ፌስቡክ ነበር ያደረኩት። በርግጥ አሁን ላይ ሳስበው ጎዞዬን በሶምሶማ ጀምሬው ቢሆን ኖሮ ይሻል ነበር እላለሁ።

“ሌዝቢያን”፣ “ኲዊር”፣ “ኢትዮጵያዊ ሌዝቢያኖች”፣ “ይኢትዮጵያዊ ሌዝቢያኖች ዴቲንግ አፕ” … እንደው ምን አለፋችሁ ያልደረደርኳቸው ቃላቶች አልነበሩም። የመጣልኝን ቃላት ሁሉ እየሞከርኩ ቢጤዎቼን ፍለጋ ቀጠልኩ። ፌስቡክ፣ ቴሌግራም፣ ጉግል ላይ ሎኬሽን ጭምር እያስገባሁ ኳተነኩኝ። ቴሌግራም ላይ ግሩፖች አግኝቼ እገባና ግን ጽሁፎችን አንብቤ ተመልሼ እወጣለሁ። መቼም ከብዙ ፍለጋ በኋላ እንደምንም ቀንቶኝ አንድ ሁለት ሰው አገኘሁ። ያዋራዋቸውን ሰዎች ስም እንኳን በስርዓት አላስታውሰውም፤ ከጉጉቴ የተነሳ ዝም ብዬ ነው ማውራት የጀመርኩት። በረጅሙ የኲዊር መንገዴ አንድ እርምጃ ተራመድኩ።

ከሆነች ልጅ ጋር ማውራት ጀመርን። እንደለመድኩት አጣደፍኩት። በሳምንት ልዩነት ቁጥሬን ላኩላት። ቴሌግራም ላይ ማውራት ጀመርን። በአጭር ጊዜ ውስጥ ፎቶ ተላከልኝ፣ ፎቶዬን ላኩኝ፣ ብዙ የግል መረጃዎቼን ላኩኝ። እንደው ምን አለፋችሁ ከአዋዋሌ ጀምሬ እስከ ሰፈሬ ድረስ ለነገ ሳልል ሁሉን ነገር ተናገርኩኝ። ቴሌግራም ላይ ወሬያችንን አጧጧፍነው። ከተዋወቅን ከወር በኋላ አንድ እሁድ ለመገናኘት ቀጠሮ ያዝን። አርብ ላይ ተቃጥረን እሁድ በጣም ሩቅ ባይባልም ለእኔ ግን ጊዜው የአመት ያህል ረዘመብኝ። ይቺን የመጀመሪያዬን ኲዊር ሴት እስካገኝ ድረስ እንቅልፍ አልወሰድ አለኝ።

አርብ ለት ከተቃጠርን በኋላ እስክንገናኝ ድረስ ላውራት ብዬ ስፅፍላት መልስ የለም። ስጠብቅ ብውልም ጠብ የሚል ቃል ጠፋ። ማውራት ብፈልግም ያው በማግስቱ እናወራለን ብዬ ተረጋጋሁ። ቅዳሜ ነግታ ብፅፍላት መልስ አትሰጥም። እንዳልደውልላት እኔ ነኝ ስልኬን የሰጠሁት። የሷ ስልክ የለኝም። ሳስበው ፍርሃት ፍርሃት አለኝ። የተላከልኝን ፎቶ ነው ያመንኩት። በስልክ አውርተን አናውቅም፤ ግንኙነታችን በሙሉ በጽሑፍ ቴሌግራም ላይ ነው። ጭንቀት ሆነብኝ። ምን አስባ ነው?

በመጨረሻ ቅዳሜ አምስት ሰዓት አካባቢ ቴክስት ደረሰኝ። “በቃ ፈርቼ ነው” የሚል። ልቤ እየፈራም ቢሆንም እኔም “ለምንድነው የፈራሽው?” ብዬ ጠየኩ። መልስ እስኪመጣልኝ ድረስ ላብ በላብ ሆንኩ። “በቃ እኔ ወንድ ነኝ ይቅርታ አድርጊልኝ በቃ ተጨነቅያለው” የሚል ሆነ መልሱ።

ምድር እንድትውጠኝ ተመኘሁ። ማን ምን ሊያደርገኝ እንደሚችል እያሰብኩ በጭንቀት ተሳቃየሁ። ምን እንደምለው ጠፋኝ። ምንስ ልለው እችላለሁ? የሰጠሁትን ኢንፎርሜሽን አሰብኩኝ። ያለ ምንም ድካም በቀጥታ ማንም ሰው ለልጁ በሰጠሁት መረጃ ሊያገኘኝ ይችላል። በፍርሃት ተውጬ ዝም አልኩኝ። ከእንግዲህ ምንም ነገር ማድረግ እንደማልችል ተቀብዬ ቁጭ አልኩ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ልጁ አዝኖ ይመሰለኛል “በጣም ይቅርታ አድርጊልኝ እንደዚህ ለማድረግ ፈልጌ አይደለም ግን ብዙ ሴቶችን ነው እንደዚህ የማደርገው እና ይህን ማድረግ ያስደስተኛል” አለኝ። ይህን ከማድረግ የሚያገኘው ጥቅም እና ደስታ ባይገባኝም

በመጨረሻ ቅዳሜ አምስት ሰዓት አካባቢ ቴክስት ደረሰኝ። “በቃ ፈርቼ ነው” የሚል።

አፌን ሰብስቤ ዝም አልኩኝ።

ብዘጋው ማንነቴን ሊያጋልጠኝ ይችላል በሚል ፍራቻ እና እንደ ጓደኛ ካየኝ ምስጢሬን ይጠብቀኛል ብዬ በማሰብ ከልጁ ጋር ማውራቱን ቀጠልኩኝ። ስልኬ ላይ መደወል ጀመረ። በእንዴት ነሽ ደህና ነሽ ተጀምሮ ፎቶውን እስከ መላክና ለወንድሜ ስራ ፈልጊለት እስከማለት ደረሰ። ፍርሃቴ አለቀቀኝም። ምን ሊለኝ እንደሚችል እያሰብኩ ጭንቀቴ ብዙም ሊለቀኝ አልቻለም። ከዚያም እንደውም ለዚህ ብቻ የሚጠቀምበት ቴሌግራም አካውንት እንዳለውና ሌሎችንም ሴቶች ላገናኝሽ ብሎ የቴሌግራም ፓስወርድ እና ዩዘር ስም ላከልኝ። ስገባ በጣም ብዙ ሴቶችን ነው የሚያወራው እንደውም እንደዛ ከሚያወራቸው ሴቶች አንዷ እዛ መጀመሪያ እሱን ያገኘሁበት አፕ ላይ ፎቶዋን አይቼው ነበር። ቴክስት አድረጌ ከልጁ ጋር መፃፃፍ እንድታቆም መከርኳት።


የቴሌግራም አካውንቱ ውስጥ ስገባ ያየሁት ነገር አሳስቦኝ ነበር። ከኔ የሚያገኘውን ኢንፎርሜሽ ከሌላ ሰው ጋር ያወራበታል፤ ከዛ ሰው ያገኘውን ኢንፎርሜሽን ከኔ ጋር ደግሞ ያወራበታል። እሱ እንኳን ምንም ባያደርግ የኔ ኢንፎርሜሽን ማን ጋር ሊደርስ እንደሚችል እና ያ ሰው ደግሞ ምን ሊያደርገው እንደሚችል ምንም የምገምተው ነገር አልነበረም።

ሳየው ልጁ “ጅንጀና” ውስጥ አልገባም። ክፋትም ያለበት አይመስልም። ጭንቀቴ ሲገባው “አይዞሽ ምንም አላደረገውም” አለኝ። ስልክ ደውሎም “በጣም ይቅርታ አድርጊልኝ አሁን አሳዘንሽኝ። ያንቺን ኢንፎርሜሽን ሁሉንም አጥፍቸዋለው ካላመንሽኝ ይኸው ራስሽ ቼክ አርጊ” ብሎ የራሱን ቴሌግራም ዩዘርኔም እና ፓስወርድ ላከልኝ። ላምነው ይከብደኛል ግን አሁን ሶስት አመት በላይ ሆኖል እስካሁን ምንምን የተፈጠረ ነገር የለም።

በዚህ ማለፉም በርግጥ እድለኛ ነኝ። ከመቸኮል እና ከመጓጓት የተነሳ የማይሆን የሩጫ መደብ ውስጥ ነው የገባሁት። የተማርኩት ትልቅ ነገር ቢኖር ሌላ ኩዊር ሰዎችን ማግኘት የማራቶን እንጂ አጭር ርቀት ሩጫ እንዳልሆነ ነው።

የተማርኩት ትልቅ ነገር ቢኖር ሌላ ኩዊር ሰዎችን ማግኘት የማራቶን እንጂ አጭር ርቀት ሩጫ እንዳልሆነ ነው።

# ከማህበራዊ ሚድያ መራቅ



ለአይምሮ ጤናዬም
ቢሆን በጣም
ጠቃሚ ሆኖ
አግኝቸዋለሁ።
በብዙ የማይጠቅም
ነገር ጭንቅላቴን
አላስጨንቀውም።

ያኔ የኩዊር ማህበረሰባችን ላይ የጥላቻ ንግግሩን ሲያሚሙቁት እኔ ሪፖርት ለማድረግ እንጂ ለሌላ ጉዳይ ብዬ የፌስቡክ አካውንቴን አልከፈተውም ነበር። ሁሉም ሰው እኛን ለመስድብ እና ለማንቆሸሽ ሲጠቀምበት እያየሁ ከነሱ ጋር መመላለስ አስፈላጊነቱ ስላልታየኝ ዝም ብዬ አልፈው ነበር።

የዛን ጊዜ የማደርገውን ነገር "digital detox" ብዬ ስም አልሰጠሁትም። ግን በተቻለኝ መጠን አካውንቴን አልከፍተውም ነበር እና ስለማልከፍተውም በዚህ በብሄርም ይሁን በወሲብ ዝናባሌ ዙሪያ ጥላቻ ላይ ባተኮሩ ንግግሮች ላይ የምሰጠው ምንም አይነት አስተያያትም ሆነ ሃሳብ አልነበረኝም።

ለስድስት ወር እካባቢ ከማህበረሰባዊ ሚዲያ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ሁኔታ ጠፍቼ ነበር። እንደውም ከመጥፋቴ የተነሳ የሚያውቁኝ ሰዎች "ደህና ነች ወይ" እያሉ ለጓደኞቼ ሁሉ ቴክስት ይልኩ ነበር።  ፌስቡክ ላይ የሚያውቁኝ ሰዎች "በህይወት አለች ወይንስ አግብታለች" ወይ ብለው መጠየቅ ድረስ ደርሰው ነበር። ብዙ አይነት ወሬዎች እና ሃሜቶችም ይሰራጩ ነበር።

እራሴን ከማህበራዊ ሚዲያ ያገለልኩት ደምሬ ቀንሼ ሳይሆን ሳላስበው ነው። በአጋጣሚ የሆነ ነገር ነው። ድንገት የዚህን ያህል ጊዜ ስልኬ ላይ ምን እሰራለሁኝ ብዬ አሰብኩኝ። በዛ ላይ ስልኬ በሳምንት የተጠቀምኩትን ጊዜ እና ምን አፕ ላይ ምን ያህል ጊዜ እንዳጠፋሁ ሲያሳየኝ ያጠፋሁት ጊዜ አሳዝነኝ። ይህን ጊዜ ለሌላ ነገር ልጠቀምበት እንደምችል አሰብኩኝ። ምንም እንኳን ባልሰራ ያን ጊዜ መፅሐፍ ላነብበት እንደምችል ታወቀኝ። እንደዚህ ያሉት ነገሮችን ሳስብ የበለጠ ማሰብ እንዳለብኝ ተገነዘብኩኝ። መፅሐፍ ለማንበብ ስሞክርም አንድ ነገር ላይ አተኩሮ የመስራት እና የመቆየት አቅሜ ምን ያህል እንደቀነሰ አየሁኝ። ምክንያቱም እነ ቲክቶክ ለረጅም ጊዜ የማተኩር አቅማችንን በጣም ጎድተውታል። ለማንበብ ስሞክርም ያታግለኝ ነበር ምክንያቱም ማተኮር ካለመቻል ውጭ ማን ምን ፖስት አድርጎ ይሆናል በሚል ሃሳብ ማህበራዊ ሚድያ አካውንቶቼን ለማየት እውሰወስ ነበር። ስለዚህ አካውንቴን ዲአክቲቬት (deactivate) አድርጌ ነው የምጠፋው ምክንያቱም በቀላሉ ለመግባት ስለማልፈልግ ነው። አካውንቴ ውስጥ ለመግባት ስራ የሚያስፈልገው ከሆነ ለማሰብም ጊዜ ስለሚሰጠኝም ጭምር ነው። ስልክ ላይ በጣም ቼክ ስለምናደርግ እርግፍ አድርጎ መተው አስቸግሮኝ ነበር። እንደውም ለስድስት ወር ሙሉ ለሙሉ ከማህበራዊ ሚዲያ ስጠፋ ስልኬን ከስማርት ስልክ ወደ ጠቅጠቅ ስልክ ቀይሬው ነበር።

እንደምንም ከተውኩት በኋላ ግን ሰላም ተሰምቶኝ ነበር። ምክንያቱም ጊዜን እዛ ላይ ብዙ ጊዜ ስናጠፋ አጠገባችን ያለ ሰውን ሁሉ እንረሳለን። አንድ ክፍል ውስጥ ሆነች ሰላም ሰላም ትባባይና እቤት ትገቢያለሽ፣ እራት ትበያለሽ፣ ከዛ ቤት ራሱ እንዳለሽ ትረሽዋለሽ ሃሳብሽ ስልክሽ ላይ ከመሆኑ የተነሳ። ከሰዎችን ጋር ራሱ ተገናኝተሽ ስልክሽ ድምጽ ባሰማ ጊዜ ሁሉ ስልክሽን ቼክ ታደርጊያለሽ እሱ ደግሞ አብሮሽ ላለ ሰው ትክክል አይደለም። በሙሉ ልብሽ አታዋሪያቸውም ሁለታችንም ደግሞ ልባችንን ስልካችን ላይ ከሆነ በአካል መገናኘታችን በራሱ ትርጉም አልባ ይሆናል። ስለዚህ አሁን ለኔ ትርጉም ያለው ግንኙነት ማለት በሙሉ ልብ አብሮኝ ካለው ሰው ጋር መሆን ነው። ይህንንም ማድረግ ችያለሁ።

ለአይምሮ ጤናዬም ቢሆን በጣም ጠቃሚ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። በብዙ የማይጠቅም ነገር ጭንቅላቴን አላስጨንቀውም። መጥፎ እና ጠቃሚ ያልሆነ ነገር (negative energy) ህይወቴ ውስጥ እንዳይመጣ አድርጋአለሁ። በሙሉ ልብ መፅሐፍ ማንበብ እና ጓደኛ ማግኘት በራሱ በጣም ሰላም ሰቶኛል። ሶሻል ሚዲያ መጠቀም ሳቋርጥ በነበረኝ ትርፍ ጊዜ በኢንተርኔት ላይ የተለያዩ ኮርሶች ለመውሰድ ችያለሁ።

ሌላም መጥፎ ነገሮችን ከራሴ አርቄያለሁ። ከኛ ማህበረሰብ ጋርም በተያያዘ ደግሞ በዋነኝነት ከሰው ጋር እሰጥ እገባ እያልኩኝ ጊዜዬን እና ጉልቤቴን

አላባክንም። ሰላሜን እንድጠብቅ አግዞኛል።

ከቻልን ሁላችንም ቢያንስ ለአንድ ወር ብናቆም ወይንም ብንቀንስ በጣም ጠቃሚ ነው ብዬ አስባለሁ። ሁሉም ሰው ጠዋት ላይ ተነስቶ ስልኩን መጀመርያ ከሚያይ ቀኑን በፀሎት ወይንም ሌላ አቅም የሚያዳብር እና መልካም ነገር ላይ በሚያውል ነገር ቢጀምር ብዬ አስባለሁ።

## እንደውም ለስድስት
## ወር ሙሉ ለሙሉ
## ከማህበራዊ ሚዲያ
## ስጠፋ ስልኬን
## ከስማርት ስልክ
## ወደ ጠቅጠቅ ስልክ
## ቀይሬው ነበር።
## እንደምንም ከተውኩት
## በኋላ ግን ሰላም
## ተሰምቶኝ ነበር።

ካትፊሽ መደረግ፥

... ከሁለት ሴቶች ጋር መተኛት ፈለገ





ፍቅር ይዞኝ ነበር። እንደው ከጊዜው አጭርነት ጋር ስንነሳ ቢያንስ በጣም በጣም ወድጄያት ነበር።

መጀመሪያ ሌዝቢያን መሆኔን እንደተቀበልኩ አካባቢ ነው። ወደ 2013 አካባቢ ይሆናል። ከመጀመሪያ ፍቅረኛዬ ጋር ከተጣላው በኋላ የሆነች ልጅን ኦንላይን ተዋወኩኝ። ያኔ ብዙም ልምድ ባይኖረኝም በተቻለኝ መጠን ሴት ልጅ መሆኗን ግን አረጋግጫለሁ።

አዲስ ሰው በመተዋወቄ በጣም ደስተኛ ነበርኩ። የበለጠ ደግሞ ያስደሰተኝ ሁለታችንም ጥሩ የሆነ ግንኙነት መፍጠራችን ነበር። ከዚህ ሁኔታ ተነስቼ ምንም ባለመጠርጠሬ ፎቶዬን ላኩላት። እውነት ለመናገር እኔ ዝም ብዬ ፎቶ ለመላክ አልድፍርም፤ መላክም አልወድም ግን ለሴቶች የተለየ ቦታ ስላለኝ ስንቀራረብ ጊዜ ደግሞ በደንብ ስለአመንኳት እና ጥርጣሬውም ስላልነበረኝ ላኩላት።

ኦንላይን ላይ ብዙ አያወራን የበለጠ ተቀራረብን፤ እኔም በፍቅር ከወደቅኩኝ በኋላ “የሆነ ጓደኛዬ አለ ላስተዋውቅሽ” አለችኝ። ከነበረን ግንኙነት አንፃር ተመልክቼ “ችግር የለውም” አልኳት እና ተዋወኩት። ጨዋታውም ምንም አይል ነበር እና ትንሽ ጊዜ አውርቼው ተለያየን። ከሷ ጋር እንዴት እንደተዋወቁ እያወራኝ ፎቶዋን ሁሉ አሳየኝ። በጣም ግራ የሚያጋባ ነገር ቢሆንም እንደዚህ ሰው ስተዋወቅ የመጀመሪያዬ ስለነበር

ባይገባኝ ነው ብዬ በዝምታ አለፍኩት። በሌላ ቀን ልጁን ድጋሚ ካላገኘሽው ብላ ስትለኝ ጉዳዩ ከሷ ጋር እንደሆነና እሱን ጭራሽ ማግኘት እንደማልፈልግ በግልፅ ነገርኳት። በጣም ተናደደች። አልሰማ ስትለኝ የኔና የሱ መገናኘት ምን እንደሚጠቅማት ጠየኳት። መልሷን ለመረዳት ረጅም ጊዜ ነበር ያስፈለገኝ።

የልጁ የልደቱ ቀን እንደነበር አስታውሳለሁ። እናም በዚህ አግኚው ሙግት መሐል እሷ በፈለገችው መንገድ አልሄድ ስላት ጉዳዩን ፍርጥ አድርጋ አወጣችው። ከልጁ ጋር የፍቅር ግንኙነት አለኝ አለችኝ። ከሷ ጋር ፍቅር ይዞኝ ስለነበር ይሄ ቢያዛዝነኝም እሱን ለምን እንዳገኘው እንደፈለገች ግን ግልፅ አላረገልኝም። እንዳልገባኝ ሲገባት ልጁ በአንድ ጊዜ ከሁለት ሴቶች ጋር አንሶላ መጋፈፍ እንደሚፈልግ እና እኔንም ለዚህ ብላ እንደሆነ የተዋወቀችኝ ነገረችኝ። ለካስ እኔ የልደቱ ስጦታ ነበርኩ።

ይህንን ሳውቅ መጀመሪያውኑ የተሰማኝን ስሜት አለማዳመጤ አናደደኝ። ልጁን የመጀመሪያ ጊዜ ሳገኘው ስለግል ህይወቴ በጣም ብዙ ጥያቄዎች ጠይቆኛል። እንደውም ከሱ ጋር ተገናኝቼ ወደ ቤት ስመልስ ለጓደኛዬ ደስ ያላለኝ ሁኔታ እንዳለ ነግሬያት ነበር። ግን ከልምድ ማነስም ይሁን በፍቅር ልቤ ከመታወሩ ምክንያት ይህንን ስሜት ችላ ብዬ መገናኘቱን የቀጠልኩብት።

ለማንኛውም አልሄድም ብዬ ድርቅ አልኩኝ። ንዴቷ ባሰ። "በቃ ፎቶሽን በፌስቡክ ላይ እለቅልሻለሁ!" አለችኝ። በጣም ፈራሁ! አንድ ሁለት ቀን በተከታታይ ታስፈራራኝ ጀመር። ምን እንደማደርግ ጭንቀት ላይ በነበርኩበት ሰአት እኔ የምኖርበት አካባቢ ላይ ኢንተርኔት ተቋረጠ። እረፍት ሆነልኝ። ከረጅም ጊዜ በኋላ ኔትወርክ ሲለቀቅ አካውንቷ እንዳለ አየሁ ግን አውርቻት አላውቅም። እሷም ምን ላይ እንደደረሰች እስካሁን ድረስ አላውቅም።

የነበረኝን ሃሳብ እና ጭንቀት ለጠላቴም አልመኘውም። ከሁሉም በላይ የሚያናድደኝ ግን ሰውን በቀላሉ እንዳላምን ስላደረገችኝ ነው። እሷን ሳገኛት ሌላ ኩዊር ሰዎችን ለመተዋወቅ የነበረኝ ጉጉት ኀይለኛ ነበር። አዲስ ስለነበርኩኝ ሁሉንም ሰው በጥርጣሬ አልመለከትም ነበር። ከሷ በኋላ ግን ኢንተርኔት ላይ ለመግባት እንኳን በጣም መጠንቀቅ ጀመርኩኝ። የሷ እና ከዛም በኋላ ያጋጠሙኝ ነገሮች አንድ ላይ ተጠቃለው ያለኝን እምነት አወርደውታል። ሰዎች የማግኘት ጉጉቴን እና ደስታዬን በጣም ቀንሶብኛል። የሷ በጣም አስፈርቶኝ ነበር ነገር ግን እንደምንም ይሄ የሷ ችግር ብቻ ነው ብዬ አልፌው ነበር። እንደምንም ብቋቋመውም አሁን ላይ ያለው ተጽዕኖ ተጨምሮ እና ተደምሮ ያለኝን እምነት ቀንሶብኛል።

# ጥንቃቄ የተሞላባቸው ስብሰባዎች



በእርግጥ አደጋዎች ቢኖሩም ከሌሎች ኩዊር ከሆኑ ሰዎች ጋር በአካል መገናኘት በጣም ነው ደስ የሚለኝ ምክንያቱም የእውነት እና ትርጉም ያለው ግንኙነት ስለሆነ ነው።

ፍቅር ይዞኝ ነበር። እንደው ከጊዜው አጭርነት ጋር ስንነሳ ቢያንስ በጣም በጣም ወድጂያት ነበር።

መጀመሪያ ሌዝቢያን መሆኔን እንደተቀበልኩ አካባቢ ነው። ወደ 2013 አካባቢ ይሆናል። ከመጀመሪያ ፍቅረኛዬ ጋር ከተጣላው በኋላ የሆነች ልጅን ኦንላይን ተዋወኩኝ። ያኔ ብዙም ልምድ ባይኖረኝም በተቻለኝ መጠን ሴት ልጅ መሆኗን ግን አረጋግጫለሁ።

አዲስ ሰው በመተዋወቄ በጣም ደስተኛ ነበርኩ። የበለጠ ደግሞ ያስደሰተኝ ሁለታችንም ጥሩ የሆነ ግንኙነት መፍጠራችን ነበር። ከዚህ ሁኔታ ተነስቼ ምንም ባለመጠርጠሬ ፎቶዬን ላኩላት። እውነት ለመናገር እኔ ዝም ብዬ ፎቶ ለመላክ አልድፍርም፤ መላክም አልወድም ግን ለሴቶች የተለየ ቦታ ስላለኝ ስንቀራረብ ጊዜ ደግሞ በደንብ ስለአመንኳት እና ጥርጣሬውም ስላልነበረኝ ላኩላት።

ኦንላይን ላይ ብዙ አያወራን የበለጠ ተቀራረብን፤ እኔም በፍቅር ከወደቅኩኝ በኋላ “የሆነ ጓደኛዬ አለ ላስተዋውቅሽ” አለችኝ። ከነበረን ግንኙነት አንፃር ተመልክቼ “ችግር የለውም” አልኳት እና ተዋወኩት። ጨዋታውም ምንም አይል ነበር እና ትንሽ ጊዜ አውርቼው ተለያየን። ከሷ ጋር እንዴት እንደተዋወቁ እያወራኝ ፎቶዋን ሁሉ አሳየኝ። በጣም ግራ የሚያጋባ ነገር ቢሆንም እንደዚህ ሰው ስተዋወቅ የመጀመሪያዬ ስለነበር ባይገባኝ ነው ብዬ በዝምታ አለፍኩት። በሌላ ቀን ልጁን ድጋሚ ካላገኘሽው ብላ ስትለኝ ጉዳዩ ከሷ ጋር እንደሆነና እሱን ጭራሽ ማግኘት እንደማልፈልግ በግልፅ ነገርኳት። በጣም ተናደደች። አልሰማ ስትለኝ የኔና የሱ መገናኘት ምን እንደሚጠቅማት ጠየኳት። መልሷን ለመረዳት ረጅም ጊዜ ነበር ያስፈለገኝ።

የልጁ የልደቱ ቀን እንደነበር አስታውሳለሁ። እናም በዚህ አግኚው ሙግት መሐል እሷ በፈለገችው መንገድ አልሄድ ስላት ጉዳዩን ፍርጥ አድርጋ አወጣችው። ከልጁ ጋር የፍቅር ግንኙነት አለኝ አለችኝ። ከሷ ጋር ፍቅር ይዞኝ ስለነበር ይሄ ቢያዛዝነኝም እሱን ለምን እንዳገኘው



እንደፈለገች ግን ግልፅ አላረገልኝም። እንዳልገባኝ ሲገባት ልጁ በአንድ ጊዜ ከሁለት ሴቶች ጋር አንሶላ መጋፈፍ እንደሚፈልግ እና እኔንም ለዚህ ብላ እንደሆነ የተዋወቀችኝ ነገረችኝ። ለካስ እኔ የልደቱ ስጦታ ነበርኩ።

ይህንን ሳውቅ መጀመሪያውኑ የተሰማኝን ስሜት አለማዳመጤ አናደደኝ። ልጁን የመጀመሪያ ጊዜ ሳገኘው ስለግል ህይወቴ በጣም ብዙ ጥያቄዎች ጠይቆኛል። እንደውም ከሱ ጋር ተገናኝቼ ወደ ቤት ስመልሰ ለጓደኛዬ ደስ ያላለኝ ሁኔታ እንዳለ ነግሬያት ነበር። ግን ከልምድ ማነስም ይሁን በፍቅር ልቤ ከመታወሩ ምክንያት ይህንን ስሜት ችላ ብዬ መገናኘቱን የቀጠልኩብት።

ለማንኛውም አልሄድም ብዬ ድርቅ አልኩኝ። ንዴቷ ባሰ። "በቃ ፎቶሽን በፌስቡክ ላይ እለቅልሻለሁ!" አለችኝ። በጣም ፈራሁ! አንድ ሁለት ቀን በተከታታይ ታስፈራራኝ ጀመር። ምን እንደማደርግ ጭንቀት ላይ በነበርኩበት ሰአት እኔ የምኖርበት አካባቢ ላይ ኢንተርኔት ተቋረጠ። እረፍት ሆነልኝ። ከረጅም ጊዜ በኋላ ኔትወርክ ሲለቀቅ አካውንቷ እንዳለ አየሁ ግን አውርቻት አላውቅም። እሷም ምን ላይ እንደደረሰች እስካሁን ድረስ አላውቅም።

የነበረኝን ሃሳብ እና ጭንቀት ለጠላቴም አልመኘውም። ከሁሉም በላይ የሚያናድደኝ ግን ሰውን በቀላሉ እንዳላምን ስላደረገችኝ ነው። እሷን ሳገኝት ሌላ ኩዊር ሰዎችን ለመተዋወቅ የነበረኝ ጉጉት ኀይለኛ ነበር። አዲስ ስለነበርኩኝ ሁሉንም ሰው በጥርጣሬ አልመለከትም ነበር። ከሷ በኋላ ግን ኢንተርኔት ላይ ለመግባት እንኳን በጣም መጠንቀቅ ጀመርኩኝ። የሷ እና ከዛም በኋላ ያጋጠሙኝ ነገሮች አንድ ላይ ተጠቃለው ያለኝን እምነት አወርደውታል። ሰዎች የማግኘት ጉጉቴን እና ደስታዬን በጣም ቀንሶብኛል። የሷ በጣም አስፈርቶኝ ነበር ነገር ግን እንደምንም ይሄ የሷ ችግር ብቻ ነው ብዬ አልፌው ነበር። እንደምንም ብቋቋመውም አሁን ላይ ያለው ተጽዕኖ ተጨምሮ እና ተደምሮ ያለኝን እምነት ቀንሶብኛል።

## “አንድ ሰው የውሸት ማንነት ይዞ እያታለለን መሆኑን በምን ማወቅ ይቻላል?

እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...

**ላያስችል** [redacted]

አንድን ነገር እውነት ነው ውሸት የሚለውን ለመረዳት ብልህ መሆን፣ ሰዎችን እንደመፅሀፍ ገልጾ የማንበብ ጥበብ ያስፈልጋል። አንድ ሰው የሚያወራው ነገር እውነት ነው ወይስ ሀሰት የሚል ጥርጣሬ ሲፈጠርብን ከዚያ ሰው ጋር በደምብ ለማውራት መወሰን አለብን። ውሸታም ሰዎች ብዙ በተናገሩ ቁጥር ቀድሞ ካወሩት ነገር ጋር የሚደነጋገር አልያም ተፃራሪ ሀሳቦችን እራሳቸው ያመጣሉ። ከዚህ በተጨማሪ በወሬ መሃል ለሚጠየቁት ማንኛውም ጥያቄ በቂ ምላሽ የማይኖራቸው መሆንና ለፈጠራ ታሪክ ጊዜ የሚወሰድባቸው፣ የሚንተባተቡም እንደሆነ አንዳች ልክ ያልሆነ ነገር አለ ማለት ነው። እንዲህ ያሉ የጥርጣሬ ስጋቶች ካሉብን ራሳችንን አደጋ ውስጥ ጥለን መንገድ መሪ፣ መስመር አመልካች ለመሆን መሞከር ከየዋህነት ያለፈ ሞኝነት ስለሆነ "ጎመን በጤና" ብለን መሰነባበቱን ብንለምድ መልካም ይመስለኛል።

**Jemes** [redacted]

መጀመሪያ የገፈቱት የfb ገፅ ምን ያህል ቆይተዋል የሚለው ነው ሰዎች ቢያዩ አመላካች ሊሆን የሚችለው ። ከዛ የጓደኞቻቸው ብዛትም ሊያሳይ ይችላል ።

በዋናነት ግን የኛና የግለሰቡ የጋራ ጓደኞች የሆኑና በአካል የማውቃቸውን መጠየቅ ጥሩ ማጣሪያ መንገድ ነው ።

# “አንድ ሰው የውሸት ማንነት ይዞ እያታለለን መሆኑን በምን ማወቅ ይቻላል?

## እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...

**Real ..[redacted]**
ከ አወራራቸው ያስታውቃል የምር በዚ ህይወት ውስጥ አሉ ወይስ እያስመሰሉ ነው የሚለው ግን ሴትም ሆና ግን በዚ ላይፍ ውስጥ ሳትኖር መስለው የሚያወሩ አሉ ይሄን ለመለየት ደሞ ግዜ ወስዶ ማውራት ቶሎ ግልፅ አለመሆን በዛላይ አካውንት ከፍተው ከ አመት በላይ በዛ አካውንት post እያደረጉ friend ያገኛሉ ከዛ text ሲልኩ ብዙ ሰው mutual friend እያዩ አይ እነዚማ በዚ ላይፍ ውስጥ ነው ብሎ ማመን አለ

**Marcella [redacted]**
ene begele catfish agatemogn yakal gn menm adergewegn or mnm chiger getemogn ayakem coz geltse eko new yeset ena yewend werea meleyet so leb alemalet enji manachenem bihon yihen mawek enchilalen gn careless selahonen new yelek egna yakaten eziw community west yale sew new

**Eldana [redacted]**
The most common one to me is they're very fast to everything like let's meet fast, let's exchange phone number fast, send pics fast and when you don't reply fast they start having meltdowns says what's wrong why aren't you replying and they don't give you space for anything like they think you will figure them out so they confuse the hell out of you and don't give space

# “አንድ ሰው የውሸት ማንነት ይዞ እያታለለን መሆኑን በምን ማወቅ ይቻላል?

## እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...

**Red F[redacted]**
Awerarachew nud pic lemelakena lemeteyek fetan nachew teyakewochachew experience lay sayhon information magegnet lay yetemeserete nw yemisetut mabrarya consistency yelewem hul gize yeteleyaye sw endemawrat nw

**Gloria [redacted]**
Mejemeria they lack the queer vibes the don't flow with the conversation,, and many stupid questions like meche nw gay yehonshiw😫😫 malet?? I was born gay,, manem ke meret tenesto gay lehun esti ayilem,, yilek real queer ppl ask meche nw ur sexuality realize yaregshiw?,, and many dump questions.. beza lay they rush to share unnecessary informations beteyekem bateyekem,, ena pic le melak tedfiya yastelashal zm belew sateyeki yelekalu kza they will ask for a complement like ik alamrem mnamn mnamn or extremely beautiful pic yilekalu,, kza yanchim laki eyalu chekchek yaregushal, ene amigne lekelish yele lmn atamgnignim ena beka betam personal details yitebekalu wr u live wr u eat wts ur phone number mnamn.. zm beteyim they'll keep on the chekechek

**Jamzee W[redacted]**
Personally catfish tederge alakm...smell them cats before fishing me my 6th sense is good on this....

Personally, I’ve never been catfished… አሳ ከማጥመዳቸው በፊት ድመቶቹን አሽትቱ። እኔ ስድስተኛ የህዋሰ አካላቴ እዚህ ላይ በጣም ጎበዝ ነው...

# “አንድ ሰው የውሸት ማንነት ይዞ እያታለለን መሆኑን በምን ማወቅ ይቻላል?

## እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...

**Below [redacted]**

እዚህ መንደር ካሉት ሰዎች ሀሳብ ጋር እስማማለሁ

1. ከአወራራቸው ያስታውቃሉ ለሁሉም ነገር ሸንቷ እንደመጣባት ነፍስ ጡር ሴት ይንቀለቀላሉ ገና በደንብ ሳትተዋቂ አካሌ ፍቅሬ ህይወቴ ሚሉ ቃላቶች ይጎርፍላቹሀል ይሄኔ የሆነ አካላቹ ከመቼው ብሎ ጥያቄ ይፈጥራል ... እመኑት

2. ገና በደንብ ሳንተዋወቅ አልባሌ ወይም ስሜት ቀስቃሽ ፎቶ እና ቪድዮ ይልካሉ እንግዲ ስሜታችሁ ጫፍ ላይ ካለ ወደ መሳሳቱ ታመራላቹ ... አድባቹ ቁጭ በሉ እንዲ ሚያረግ ዜጋ የለም ቢኖርም አይጠቅማችሁም ቅንዝራም አለመሆን ወይ ስሜትን መቆጣጠር አሪፉ ነገር ነው

3. voice ላኩ ሲባሉ ያንቃቸዋል በቃ ያቅለሸልሻቸዋል ግግም ስትሉባቸው ደህና አደርሽ" ስትሉ `ትላንት ነበር ሰርጌ" የሚል ከወሬያቹ ጋር ማይገናኝ መልስ የሆነች ቆንጆዬ ድምፅ ያላት ሴትን voice ይልካሉ... መፍትሄውም ደጋግሞ ማስላክ ነው ከአንድ ሰው 10 አይነት ቆንጆዬ ድምፆች ይላኩልናል እና አሁንም ይሄን ሰው block ወይ ignore መግጨት ካልቻልሽ ችግር አለብሽ ተመርመሪ

4. Ignore ሲገጩ ወይ ዝም ሲባሉ አስሬ ይልካሉ ምክንያቱም ሚፈልጉት ነገር ስላለ አይፋቱሽም... ሞኞ ተፈቅሬ ወይ ተወድጄ ነው ብለሽ እንዳታስቢ የት አውቆሽ 👀 መቼም በአንድ ሰአት ትውውቅ አትይኝም ሚሻልሽ መሮጥ ነው አዎ ወደ Block መስመር እሩጪ 🏃‍♀️➡️🏃‍♀️➡️🏃‍♀️➡️🏃‍♀️➡️

5. የሆነ ታሪክ ላይ ይቀባጥራሉ ውሸት ያው ውሸት ስለሆነ ሙሉ እውነተኛ ታሪክ አይናገሩም ... አሁን ስድስተኛ የስሜት ህዋስሽን እመኚው

6. ....እያስታወስኩ ካለ እጨምራለሁ እየር ልቀበል 😁🙏